


# *የሀገር ባለውለታዎች እና ታላላቅ ጀግኖቻችን የተዘከሩበትን- 'ያልታደለች ሀገር፣ ሕዝብ እና ሰራዊት' መጽሐፍ አጭር ዳሰሳ*

*በተረፈ ወርቁ*

## 1. እንደ መግቢያ፡-

*"Old soldiers never die; they just fade away."* (Gn. Douglas Macarthur)

በአሜሪካ ታሪክ የመጀመሪያው ባለ አምስት ኮከብ የጦር ጄኔራል እና የአሜሪካ ጦር ኃይሎች ዋና ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ፊልድ ማርሻል ዳግላስ ማካርተር ሀገራቸውን በወታደርነት ስላገለገሉ የቀድሞ የጦር አባላት ወታደሮች እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር፡፡ 'Old soldiers never die; they just fade away.' በርግጥም ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ጥቅም ሲሉ ውድ ሕይወታቸውን መሥዋዕት ለማድረግ ቃል ኪዳን ለገቡ፣ በቃልም ሆነ በተግባር በሀገርና በሕዝብ ፍቅር ለታሠሩ፣ በላባቸው፣ በእንባቸውና በደማቸው ሕያው ታሪክን ያቆዩልን ወታደሮች ጄኔራል ማካርተር እንዳለው፣ 'ቢደክሙ' እንጂ ሞትንማ- ለሀገራቸው፣ ለሕዝባቸው ባላቸው ፍቅርና በከፈሉት ትልቅ መሥዋዕትነት ድል ነሥተውታል፡፡

እናም ይህን እውነታ መሠረት ባደረገ መልኩ የግርማዊ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እና የደርግ የጦር ሰራዊት የቀድሞ አባል፣ የጦር መሪ፣ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንን እና ታንከኛ ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱ 'ከሠላሳ ዓመታት በላይ በተለያዩ የጦር ግንባሮችና የጦር ክፍሎች ያደረጉትን አገልግሎታቸውን፣ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የከፈሉትን መሥዋዕትነት በተመለከተ 'ዕጣ ፈንታ እና መሥዋዕትነት' ተከታይ የሆነ ሁለተኛ መጽሐፋቸውን፣ 'ያልታደለች ሀገር፣ ሕዝብ እና ሰራዊት' በሚል እንካችሁ ብለውናል፡፡

## 2. ታሪክ ትምህርት ቤት ነው፡-

የሀገረ አሜሪካ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት የነበሩት ባራክ ኦባማ፣ የጥቁር አፍሪካ አሜሪካውያን የታሪክ፣ የቅርስና የባህል መታሰቢያ ቤተ-መዘክር/ሙዚየም በተመረቀበት እለት ባደረጉት ንግግራቸው እንዲህ ብለው ነበር፣ ‘የቀደመ ታሪኩን የማያውቅ ሕዝብና ሀገር ስር እንደሌላው ዛፍ ይቆጠራል፡፡’ በመሠረቱ የታሪክ ትምህርትና እውቀት ለአንድ ሀገርና ሕዝብ ዕድገት ቁልፍ ሚና እንዳለው ብዙዎች ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ በርግጥም ደግሞ የቧላ ታሪኩን የማያውቅ ሀገርና ሕዝብ ዛሬው ጉዞውን በትክክል ለመራመድና የነገውን ጉዞውን በተስፋ አጥርቶ ለማየት እንደሚቸገር እሙን ነው፡፡

ባለፉት ጥቂት ዓመታት እያስተዋልነው እንዳለነው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ የነበራቸው በተለያየ የሥራ ኃላፊነት ላይ፣ በሲቪልና በሚሊታሪ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩ ሰዎች እያወጧቸው ያሉት መጽሐፎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መምጣታቸው መልካም ዜና ነው፡፡ አብዛኛው የትናንትናው ትውልድ ታሪክና ረጅም የትግል ጉዞውና መሥዋዕትነቱ በወጉ ባልተቀመረበትና በስፋት ባልቀረበበት ኹኔታ እንዲህ ዓይነቶቹ መጽሐፍት መታተም ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ አያጠራጥርም፡፡ በዚህ ረገድም የትናንትና ታሪካችን የተሟላና ሙሉ ቅርጽ የያዘ እንዲሆን ለሚደረገው ጥረት ጥሩ አበርክቶት እንደኾነ በግሌ አምናለሁ፡፡

‹‹ታሪክ ትውልድ መሸጋገሪያ ድልድይ ነው!›› እንዲሉ አበው፣ በተጨማሪም የዛሬው ትውልድ የትናንትናው ትውልድ፣ ጀግኖች አባቶቹና እናቶቹ ስለ አገራቸውና ወገናቸው የነበራቸውን ፍቅርና ተቆርቋሪነት፣ የከፈሉትን መሥዋዕትነት፣ ያለፉባቸውን ውጣ ውረዶችና ጠመዝማዛ መንገዶች፣ ብርታታቸውንና ድካማቸውን፣ ቁጭታቸውንና ብሶታቸውን፣ ድልና ሽንፈታቸውን፣ ከብረት የጠነከረ ወኔያቸውን፣ ጀግንነታቸውንና ብርቱ ተጋድሎአቸውን፣ ርእያቸውንና ተስፋቸውን … እንደ መስታወት የሚያሳዩ በመሆናቸው የእንዲህ ዓይነቶቹ የታሪክ መጻሕፍት መውጣት መበራከት ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡

ስለሆነም ትናንትና የሀገር ባለውለታ የሆኑ ጀግኖቻችን ትውልድ ታሪካቸውን በሚገባው ፍቅርና ክብር እንዲዘክረውና ቋሚ የሆነ መታሰቢያ እንዲደረግላቸው በማሰብ፣ ኩሩው ኢትዮጵያዊ፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እጅ የኦጋዴን ጦርነት ከፍተኛውን ቅዱስ ጊዮርጊስ

ጦር ሜዳ የጀግና ሜዳይ ተሸላሚ፣ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንን፣ ታንከኛ ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱ በብዙ ድካምና ልፋት ላበረከቱልን ለዚህ ሁለተኛ መጽሐፋቸው በግሌ ላመሰግናቸውና እንኳን ደስ አልዎ ልላቸው እወዳለሁ!!

ጄኔራል ዋሲሁን 'ያልታደለች ሀገር፣ ሕዝብ እና ሰራዊት' በሚል ርእስ ያቀረቡልን ሁለተኛ መጽሐፋቸው መግቢያውን እና ማጣቃሻዎችን/References ጨምሮ በ296 ገጾች የተቀነበበ ነው፡፡ ጄኔራሉ በተጨማሪም በመጽሐፋቸው ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ለዓለማችን ታላላቅ መሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የጻፏቸውን ደብዳቤዎች በአባሪነት አካተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በኢትዮጵያ፣ በአፍሪካና በመላው ዓለም ሰላም ይሰፍን ዘንድ፣ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ለነበሩት ለኮፊ አናን፣ ለአሜሪካው ፕሬዚደንት ለባራክ ኦባማ፣ ለኩባው ፕሬዚደንት ለፊደል ካስትሮ የጻፏቸው የመልካም ምኞት መግለጫዎችና የሰላም ምኞት ደብዳቤዎቻቸው ይጠቀሳሉ፡፡

ጄኔራል ዋሲሁን ይህን ሁለተኛ መጽሐፋቸውን መታሰቢያነቱን፣ በኢሕአዴግ መንግሥት ትእዛዝ ለ10 ዓመታት በግፍ ታሰርው በቆዩባቸው ጊዜያት ከባድ የሆነ ችግርና መንገላታት ለደረሰባቸው፣ ከጎናቸው ሳይለዩ አብረዋቸው በመንፈስ ለታሰሩት፣ እናትም ሚስትም ሆነው ያን የመከራ ዘመን በጽናት አብራዋቸው ለቆሙት ለውድ ባለቤታቸው ለወ/ሮ መአዛ መሸሻ እና ለልጆቻቸው ይሆን ዘንድ አበርክተውልናል፡፡

በተጨማሪም ጄኔራል ዋሲሁን ይህ መጽሐፋቸው፣ ኢትዮጵያ ሀገራችን ዳር ድንበሯ ተከብሮና አንድነቷና ህልውናዋ ተጠብቆ፣ ታፍራና ተከብራ በነጻነቷ እንድትኖር ሲሉ ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ፣ መተኪያ የሌላትን ውድ ሕይወታቸውን በየጦር ግንባሩ ለሠዉ፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ልዑላዊነት ክቡር ደማቸውን ላፈሰሱና አጥንታቸውን ለከሰከሱ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ሁሉ እንዲሆን አበርክተዋል፡፡

### 3. ደራሲውን ብ/ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱን በጥቂቱ፡-

በቀድሞ የወለጋ ጠቅላይ ግዛት በሆሮ ጉዱሩ አውራጃ በ1933 ዓ.ም. የተወለዱት በብ/ጄ ዋሲሁን ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ድረስ በዛው በትውልድ ሀገራቸው በወለጋ በማጠናቀቅ በ1953 ዓ.ም. የሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤትን ተቀላቀሉ፡፡ ጄኔራሉ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከተማሯቸው ትምህርቶች መካከልም፣

የታንከኛ መሠረታዊ ትምህርት፣ ከፍተኛ የውጊያ መረጃ ትምህርት፣ የአውሮፕላን የአየር ቅኝት/፣Air Reconnaissance ፀረ-የአየር በረራ ጠለፋ/Anti-Hijack፣ በአሜሪካ ፎርትኖክስ ኬታንኪ ከፍተኛ የታንክ ትምህርት፣ በአሜሪካ ኦክላሃማ ፎርት ሲል የኅብርት ውጊያ እና በራሺያ ቬስትራል የጦር አካዳሚ ከፍተኛ ታንክ ሜካናይዝድ ትምህርት ይገኙበታል፡፡

ብ/ጄ ዋሲሁን ንጋቱ በኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስቴር የቀድሞ ሰራዊት ውስጥ በተለያዩ የጦር ግንባሮችና የጦር ክፍሎች ለ30 ዓመታት ሀገራቸውን በማገልገል ወታደራዊ ግዳጃቸውን በብቃትና በትጋት ለመወጣት የሞከሩ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንን ናቸው፡፡ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ላደረጉት ውለታም፣ የኦጋዴን ጦርነት ከፍተኛውን ቅዱስ ጊዮርጊስ ጦር ሜዳ የጀግና ሜዳይ ባለዘንባባ ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እጅ ተቀብለዋል፡፡ ብ/ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱ በውጭ ሀገር በአውሮፓ፣ በእስያ እና በሀገራችን የተለያዩ ግዛቶች- በኦጋዴን፣ ሐረር፣ በኤርትራ አስመራ፣ በትግራይ፣ በወሎ፣ በጎንደርና በባሕር ዳር ሀገራቸውን በተለያዩ ወታደራዊ ግዳጆች አገልግለዋል፡፡

ከደርግ ሰራዊት መበተን በኋላ ለ10 ዓመታት በአዲስ አበባና በመቀሌ ታስረዋል፡፡ በአሁን ሰዓት በጡረታ ላይ የሚገኙት ብ/ጄ ዋሲሁን ንጋቱ በሰላምና በዕርቅ፣ በበጎ አድራጎት ውስጥ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም በተለያዩ ሕዝባዊ መድረኮች ላይ በመገኘት ስለሀገር ፍቅር፣ ስለ ነጻነት ክብርና ኩራት ወኔ ቀስቃሽ የሆኑ ንግግሮችን ያደርጋሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ጄኔራል ዋሲሁን የኢትዮጵያ ባለውለታ ሆኑ አርበኞችና የጦር ጀግኖች በሕዝብ ዘንድ እንዲታወሱና በመንግሥት በኩል ቋሚ የሆነ መታሰቢያ እንዲደረግላቸው የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ ያሉ ኩሩ ኢትዮጵያዊ፣ ከፍተኛ የጦር መኮንን ናቸው፡፡

## 4. ጀግኖቻችንና ባለውለታዎቻችን እናስታውሳቸው፡-

ጄኔራል ዋሲሁን በመጽሐፋቸው ውስጥ አርአያና ተምሳሌት ከሆኗቸው ጀግኖች አርበኞች ጀምሮ ከሠላሳ ዓመታት በላይ ሀገራቸውን በተለያዩ ወታደራዊ ግዳጆች ባገለገሉባቸው ዘመናት አብረዋቸው የነበሩትን የጦር ጓዶቻቸውን፣ በጀግንነታቸው፣ በአዋጊነታቸው፣ በአመራር ችሎታቸውና ብቃታቸው የሚያደንቋቸውን ጀግኖችን- በኢትዮጵያዊነት ጠንካራ የአንድነት መንፈስ፣ ፍቅር፣ ወኔ፣ ብርታትና ቁጭት በርካታ ጀግኖቻችንና ባለውለታዎቻችንን በዚሁ መጽሐፋቸው ውስጥ ለማንሳት ሞክረዋል፡፡

ከአምስቱ ዓመት ታዋቂ አርበኛ፣ የፋሽስት ጣሊያንን ሰራዊት ካረበደበዱት ጀግና፣ የጦር መሪ ከነበሩት ከሌፍተናንት ጄኔራል ጃጋማ ኬሎ ጀምሮ ራስ መስፍን ስለሺ፣ ወንድማማቾቹን አርበኞች ደጃዝማች አበበና ተሾመ ሸንቁጥን፣ ከኦጋዴን የጦር ግንባር ጀግና ከነበሩት ብ/ጄ ጥላሁን ደምሴ፣ ብ/ጄ ካሣዬ ጨመዳን እና 'የአየር ላይ ነብር' በመባል የሚታወቁትን ብ/ጄ ለገሰ ተፈራ፣ በሰሜን ግንባር እንደ ዐፄ ቴዎድሮስ ለሀገራቸው ክብር ሲሉ ራሳቸውን የሠዉትን፣ ጄ/ል ተሾመ ተሰማ፣ ብ/ጄ ተመስገን ገመቹ፣ ኮ/ል ካሣ ገ/ማርያም የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን ታላላቅ ጀግኖች ገድላቸውን አውስተዋል፡፡

ጄ/ል ዋሲሁን በመጽሐፋቸው ውስጥ ከሴት አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ እስከ ተወዳጇ አርቲስት ብዙነሽ በቀለ ተካተዋል፡፡ በነገራችን ላይ ቡዝነሽ በቀለ በ1967 ዓ.ም. ጆሮዋን ለመታከም ወደ አሜሪካ አምርታ ነበር፡፡ እናም ሕክምናዋን አጠናቃ እግረ መንገዷን ጣሊያንን ለመጎብኘት ወደ ሮም መጥታ ነበር፡፡ ብዙነሽን በሮም ቆይታዋ በእንግድነት የተቀበሏት በጊዜው በሮም ኢትዮጵያ አየር መንገድ የደህንነት ጥበቃ ኃላፊ የነበሩት የአሁኑ ብ/ጄ ዋሲሁን ነበሩ፡፡ ታዲያ በአንድ አጋጣሚ ብዙነሽ ከአንድ ኢጣሊያዊ ጋር ተቀምጣ ሲነጋገሩ ይደርሳሉ፣ የዛን ጊዜው ሻለቃ ዋሲሁን ብዙነሽን ተገርመው ሲመለከቷት ብዙነሽ ሻለቃ ዋሲሁንን እያየች ይኸውልሆ አንድ ሰላቶ ጣሊያን በሰላም ማርኬ ቆየሁዎ በማለት ፈገግ እንዳሰኘቻቸው በዚሁ መጽሐፋቸው ውስጥ አንስተውታል፡፡ (ገጽ 138)

ጄኔራሉ በመጽሐፋቸው ውስጥ በትውልዱ ኤርትራዊ በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ስለነበረውና ሀገራችን በፋሽስት ኢጣሊያ በተወረረችበት ወቅት የጥቁር አንበሳ ጦርን በመቋቋም አኩሪ ተጋድሎ በመፈጸም ትልቅ ታሪክ ለፈጸመው ለወጣቱ ጀግና ለኮ/ል በላይ ኃይለ አብ፣ ለእነ ጄ/ል ጃጋማ ኬሎ፣ ለጀግኖች አርበኛ አባቶችና እናቶች፣ ሀገራቸውን በአፍሪካና በዓለም መድረክ ስሟን ላስጠሩ ጀግኖች፣ እንዲሁም ለቀድሞ ለኢትዮጵያ ወታደሮች የመታሰቢያ ሐውልት እንዲቆምላቸውና እንዲሁም በየትኛውም የሙያ መስክ የሀገር ባለውለታ ለሆኑ ጀግኖቻችን ትውልድ እንዲዘክራቸውና ተገቢውን ክብር እንዲያገኙ በመንግሥት በኩል መሠራት እንዳለበት በዚሁ መጽሐፋቸው ውስጥ በአጽንኦት ገልጸዋል፡፡

ጄኔራሉ አብረዋቸው በእስር ቤት ከነበሩት ከዕውቁ ሐኪም ከፕ/ር አስራት ወልደየስ ጀምሮ በአሁን ወቅት የዮድ አቢሲኒያ የባህል ምግብ አዳራሽ ባለቤት ከሆኑት የዛን ጊዜው መቶ አለቃ ኮሬ የአሁኑ አቶ ትእዛዙ ኮሬ አንስቶ… የእስር ቤት ቆይታ አሳዛኝ፣ አስገራሚ፣ አስቂኝና አይረሴ የሆኑ ትዝታቸውን፣ ተስፋቸውን፣ ቁጭታቸውን፣ ብሶታቸውን፣ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ያላቸውን ሕልማቸውንና መልካም ምኞታቸውን፣ በኢትዮጵያ አምላክ ላይ ያላቸውን ጽኑ እምነታቸውን፣ የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ገጠመኞቻቸውን ቀለል ባለ ቋንቋና ለዛ ባለው ስሜት በመጽሐፋቸው አጋርተውናል፡፡

## 5. ያልታደለች ሀገር፣ ሕዝብና ሰራዊት፡-

ጄ/ል ዋሲሁን ይህን መጽሐፋቸውን በስጦታ ባበረከቱልኝ ወቅት በመጽሐፋቸው ዙሪያ ስንነጋገር የመጽሐፋቸውን አርእስት ይህ እንዲሆን ለምን እንደመረጡ ጠይቄያቸው ነበር፡፡ ምክንያታቸውን ቢያስረዱኝም ለእኔ ግን ለመቀበል ቸግሮኝ ነበር፡፡ ጄኔራሉ *'ዕጣ ፈንታና መሥዋዕትነት'* ከሚለው መጽሐፋቸው በማስከተል ያስነበቡን ይህ ሁለተኛው መጽሐፋቸው የሰጡት አርእስት፣ ሀገሪቱ ዕድለ ሰባራ/እጀ ሰባራ፣ ፈጢሪ የዘነጋት የምትመስል፣ የወላድ መካን የሆነች፣ ሕዝቦቿና የቀድሞው ሰራዊትም ያልታደለ እንደሆነ በመቁጠር- የመጽሐፋቸውን አርእስት- የኀዘንና የቁጭት ስሜት ያየለበት የሚመስል ተስፋን፣ ፍቅርን ብርሃንን ከመሰበክ ይልቅ ተብሰልሳይ፣ ቆዛሚና መጽሐፉ በውስጡ ከያዘው ዐቢይ መልእክት/በጎ ሐሳብ ጋር ብዙም የማይጣጣም ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡

በተጨማሪም የዚህ መጽሐፍ ደራሲ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየተካኼደ ያለውን ለውጥ ደጋፊ፣ የሰላምና የዕርቅ እንዲወርድ የሚማጸኑ፣ በታሪካችን የሆነውን ክፉ የታሪክ ዘመናት በይቅርታ ዘግተን፣ ቂም በቀልን ሽረን በነጻነቷ፣ በአንድነቷ ኩሩና ጠንካራ ሆነች፣ በረሃብና በጦርነት ሣይሆን በሰላሟ፣ በኢኮኖሚ ብልጽግናዋ ለአፍሪካና ለዓለም ተምሳሌት የሆነች ሀገርን ለነገው ትውልድ እናውርስ የሚሉ ዕርቀ-ሰላምን፣ ተስፋን ሰባኪ ከመሆናቸው አንጻርና በመጽሐፋቸው ውስጥ በርካታ ኢትዮጵያውያን ጀግኖችንና ባለውለታዎችን ከመዘከራቸው አንጻር የመጽሐፋቸው አርእስት ሌላ ቢሆን ተመራጭ ይሆን ነበር፡፡

በርግጥ ያ ለአፍሪካ ኩራት ይሆናል የተባለ ሠራዊት ዕጣ ፈንታው በስተመጨረሻ ሜዳ ላይ መበተን ምናልባትም ያልታደለ ሊያሰኘው ቢችልም ከነጀግንነቱና ከነኩራቱ፣ ከብርታቱና

ከድካሙም ጋር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የራሱ የሆነ ደማቅ አሻራ እንዳለው ግን የሚያከራክር ጉዳይ አይመስለኝም፡፡ ታሪኩ የሽንፈትም ይሁን የድል ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ነጻነትና ልዑላዊነት፣ ለሕዝቦቿ ክብርና ፍቅር ሲሉ ውድ ሕይወታቸውን የሠዉ ጀግኖችን ታሪክና ትውልድ ሁሌም አይዘነጓቸውም፡፡ ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ላሰምረበት የምፈልገው ዐቢይ ቁም ነገር የቅርብ ዘመናት ወይም በደርግ ዘመናት የተካኼዱ የጦርነት/የወታደራዊ ዘመቻ ታሪኮቻችንን ስንመለከት በወንድማማች ሕዝቦች መካከል የተደረገ የእርስ በርስ ጦርነት በመሆኑ- በክብርና በኩራት የምንተርከው ታሪክ ከመሆን ይልቅ በጸጸት የምናስታውሰው፣ በእፍረት የምንሸማቀቅበት የመሆኑን ጉዳይ ነው፡፡

አስገራሚውና አስደናቂው ነገር የታሪክ ድርሳናትም እንደሚመሰክሩት ሀገራችን ካሳለፈቻቸው በርካታ የእርስ በርስ ጦርነቶች፣ ካሳለፈቻቸው በርካታ ውስብስብ ታሪክ ሂደት አንጻር እንደ ሀገር ዛሬም መቀጠሏ ብዙዎችን ያስገርማቸዋል፡፡ ዕውቁ የታሪክ ምሁር ፕ/ር ባሕሩ ዘውዴ በ1997 የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማኅበር ‘በ2020 የምናልማት ኢትዮጵያ’/‘Vision 2020’ በሚል ባዘጋጀው መድረክ ላይ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፋቸው እንደገለጹት፣ ‘ኢትዮጵያ በታሪኳ ያመለጧትን የ’ለውጥ ዕድሎች’ን በማንሳት በእነዚህ ‘የለውጥ ዕድሎች’ ሀገሪቱ ሳትጠቀምባቸው በመቅረት ለከፋና ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምስቅልቅል ቢዳርጓትም ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ጠፋች፣ አሁንስ አለቀላት ሲባል ዳግመኛ እንደ ሀገር መቀጠል የቻለችበትን የትንሣኤ ታሪኳን- ከሕዝቦቿ የሃይማኖተኝነትና ሀገሪቷ ከረጅም ዘመን ታሪኳ ካካበተችው ወድቆ የመነሳት የአይበገሬነት ጠንካራ ባህልና ጥብቅ የሕዝቦቿ ማኅበራዊ ትስስር ጋር በማቆራኘት፣’ የሰጡትን ምሁራዊ ትንታኔያቸውን ያስታውሷል፡፡

ደራሲው በመጽሐፋቸው መደምደሚያ ላይ የሀገራችንን የኢትዮጵያን መፃኢ ዕድል ተስፋ ያለው፣ ብሩሕና መልካም ለማድረግም ዕርቀ-ሰላም፣ አንድነትና ፍቅር፣ ፍትሕና ይቅር ባይነት በቃል ባለፈ በሁሉም ዘንድ ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡ መንግሥትም ሆነ ተፎካካሪ ፓርቲዎች አንድ ሀገር ዜጎች- ኢትጵያውያን በመሆናቸው፣ ለሀገራቸው ጥቅምና ለሕዝቦቿ ብልጽግና ሲሉ- በአንድነት፣ በእኩልነትና በሰላም ለመሥራት የአመለካከትና ሐሳብ ልዩነታቸውን በመነጋገርና በመወያየት በማጥበብ፣ በጋራ መሥራትና መኖር ካልተቻለ በዚህች ሀገር ዕድገትና ሰላም ለማምጣት እንደማይቻልም ያሳስባሉ፡፡ (ገጽ 173-182)

## 6. እንደ መውጫ፡-

በብ/ጄ ዋሲሁን ንጋቱ፣ **'ያልታደለች ሀገር፣ ሕዝብ እና ሰራዊት'** በሚል አርእስት ባበረከቱልን መጽሐፋቸው ላይ ያደረኩትን አጭር ዳሰሳና የግል አስተያየቴን ጄኔራሉ በመጽሐፋቸው ውስጥ ባሰፈሩትና የሥራ ባልደረባቸውና ጦር ጓዳቸው በሆኑት በሜጀር ጄኔራል ሁሴን አህመድ ጠቃሚ ምክር ለመደምደም ወደድኩ፣

*ሕይወት ብዙ ውጣ ውረድ አላት፡፡ ክፉም በጎም ይፈራረቁብናል፡፡ ተቃራኒ ስሜቶች ይቀራመቱናል፡፡ የእኔም ሕይወት እንደብዙዎቹ የጦር ጓዶች ሁሉ ጉዞዬ በሬትና በማር የተሞላና የተለወሰ ነው፡፡ አብዛኛው የሬት ጉዞ እኛው ሰዎች የፈጠርነው ነው፡፡ ሰው ከእንሰሳት ሁሉ የላቀ ነው ይባላል፡፡ እውነትም የሚሠራው የሳይንስና የቴክኖሎጂ እመርታ ተአምር የሚያሰኝ ነው፣ የፍቅር ስሜቱም እጅግ የመጠቀ ነው፡፡*

*ነገር ግን አለመግባባቱን በጥበብና በትዕግሥት፣ በውይይትና ቀርቦ በመነጋገር በሰላማዊ መንገድ መፍታት እየተሳነው በተለያዩ ሰበቦች ሁከት እያነሳ የጥበብና የፍቅር ውጤቶችንና ስሜቶችን የሚያውድም ግጭት እየፈጠረ እንደተራበ ተኩላ እየተነካከሰ ራሱንና አካባቢውን በጦርነት ያወድማል፡፡ ለዚህም እኛ የዓይን ምስክሮች ነን፡፡*

*ኢትዮጵያ ሀገራችን የተፈጥሮ ሀብትና ውበት ሳታጣ ለዘመናት የጦርነትና ጉስቁልና (የድህነት) መድረክ ሆና አየናት፡፡ ምነው ቢበቃ!! ምነው በሆድ ሳሆን በጭንቅላት እያሰብን ሰላምንና ፍቅርን ብንላበስ?! ምነው ለምንወልዳቸው ልጆች ሰላምን ፍቅርን ዕድገትን ብናወርሳቸው?! እየወለድን ለጦርነትና ለድህነት! ማር ማውረስ ተስኖን ሬት የምናወርሳቸው ከሆነ መውለድን እናቁም!!*

**ሰላም!!**